U.S. Department of Housing and Urban Development
Office of Housing Office of Multifamily Housing Programs

# የፍሬ ነገር ሰነድ

## በኤችዩዲ ለሚረዱ ነዋሪዎች

## የኪራይ እርዳታ ክፍያዎች (አርኤፒ)

## "የኪራይዎ መጠን እንዴት እንደሚወሰን"

**የመኖሪያ ቤቶች ቢሮ**

****ጁን 2007****

*ይህ የፍሬ ነገር ሰነድ የቤት ባለቤቶች/የአስተዳደር ወኪሎች (ኦኤ) እና በኤችዩዲ ድጋፍ የሚረዱ ነዋሪዎች ገቢያቸውን መግለጽንና ማረጋገጥን በሚመለከት ያላቸውን መብትና ኃላፊነት የሚገልጽ አጠቃላይ መመሪያ ነው።*

## ገቢንና ኪራይን በትክክል መወሰን ለምን ዋና ነገር እንደሆነ

የቤቶችና ከተማ ልማት ክፍል ጥናቶች ትክክል ያልሆነ ኪራይ የሚከፍሉ ብዙ ነዋሪዎች ቤተሰቦች እንዳሉ ያሳያሉ። ለዚህ ችግር ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው:

- በነዋሪ ቤተሰቦች በኩል ገቢን አሳንሶ ማሳወቅ እና
- የቤት ባለቤቶች ወኪሎች ከተጠያቂነት ነፃ የሆኑ ነዋሪ ቤተሰቦችን ነፃ አለማድረግ ወይም ቅናሽ አለመስጠት ናቸው።

የባለቤቶች ወኪሎችና ነዋሪዎች ሁሉም ትክክለኛው ኪራይ መከፈሉን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።

**የባለቤቶች ወኪሎች ኃላፊነቶች:**

- ትክክለኛ የገቢ መረጃ ማግኘት
- የነዋሪዎችን ገቢ ማጣራት
- ነዋሪዎች የሚገባቸውን ከተጠያቂነት ነፃ መደረግ ወይም ቅናሽ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ
- የተከራይን የኪራይ መጠን በትክክል ማስላት
- የኪራይ ስምምነትን፡ የገቢንና የኪራይ የውሳኔ ኮፒን ለተከራዮች መስጠት
- በቤተሰቡ አባላት ቁጥር ማናቸውም ለውጥ በሚኖርበት ጊዜ የኪራዩን ስሌት እንደገና መሥራት
- የነዋሪዎች ገቢ ሲቀንስ የኪራዩን ስሌት እንደገና መሥራት
- የነዋሪ ገቢ በወር $200 ወይም ከዚያ በላይ ሲጨመር የኪራዩን ስሌት እንደገና መሥራት
- ሲጠየቅ ስለ ባለቤት ወኪሎች ፖሊሲዎች መረጃ መስጠት
- ገቢን ስለ ማስታወቅ ወይም ኪራይን ስለ መወሰን ግዴታዎች ወይም አሠራሮች ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ለውጥ ለነዋሪዎች ማስታወቅ

**የነዋሪዎች ኃላፊነቶች:**

- የቤተሰባቸውን ብዛት ትክክለኛ መረጃ መስጠት
- ማናቸውንም ገቢ ማስታወቅ
- ገቢና ወጪን የሚመዘግቡ ወረቀቶችን፡ ቅጾችንና ደረሰኞችን ቅጂ ማስቀመጥ
- በዓመታዊ የገቢ እንደገና ማረጋገጫ ጊዜ መካከል የደረሰን የቤተሰብ ብዛትና የገቢ ለውጥን ማሳወቅ
- የገቢ ማጣሪያ ፈቃድ መስጫ ቅጾችን መፈረም
- የኪራይ ግዴታዎችንና የቤቱን ደምቦች መከተል

## የገቢ አወሳሰን

የአንድ ቤተሰብ የሚጠበቅ ያልተጣራ የገቢ መጠን የቤተሰቡን እርዳታ የማግኘት ብቻ ሳይሆን ቤተሰቡ የሚከፍለውን የኪራይ መጠንና የሚያስፈልገውን የድጎማ መጠን ይወሰናል፡፡ የሚጠበቀው ገቢ ከተጠያቂነት ነፃ መደረግን ወይም ቅናሾችን ግምት ውስጥ በማስገባት ቤተሰቡ በሚቀጥሉት አሥራ ሁለት (12) ወራት የሚከፍለውን ኪራይ ለመወሰን ይሠራበታል፡፡

**ዓመታዊ ገቢ ምንድን ነው?**

ያልተጣራ ገቢ – ከገቢነት የሚገለሉ = ዓመታዊ ገቢ

**ማስተካከያ የተደረገበት ገቢ ምንድን ነው?**

*ዓመታዊ ገቢ* – *ተቀናሾች* = *ማስተካከያ የተደረገበት ገቢ*

## ተከራይን የኪራይ መጠን መወሰን

የኪራይ ክፍያ አርዳታ (አርኤፒ) የኪራይ ቀመር፡ አንድ ቤተሰብ የሚከፍለው የኪራይ መጠን ከሚከተሉት እጅግ ከፍተኛ የሆነውን ነው፡

- *ማስተካከያ* የተደረገበትን የቤተሰቡን የወር ገቢ 30%
- የቤተሰቡን የወር ገቢ 10%
- የእርዳታ ኪራይ ወይም ቤተሰቡ ኪራይ መክፈል እንዲችል ከድርጅት የሚያገኘውን እርዳታ ክፍያ።
- ማስገንዘቢያ: **አንድ አከራይ ለኪራይ ለአርኤፒ ፕሮግራም አመልካችን ተቀብሎ የሚያስገባ የተከራዩ ጠቅላላ የኪራይ ክፍያ ከተከራየው ቤት ጠቅላላ የኪራይ መጠን የሚያንስ ከሆነ ብቻ ነው።**

## ገቢና ንብረቶች

በኤችዩዲ የሚረዱ ተከራይ ነዋሪዎች ከማናቸውም ምንጭ የሚያገኙትን ማናቸውንም ገቢ ለቤቱ ባለቤት ወይም ወኪል (ኦኤ) ማስታወቅ አለባቸው። ገቢ የማይመለከታቸውና የኪራይ ዋጋ ቅናሽ የተከራይ የቤት ኪራይ አሠራር አካል ናቸው።

በዓመታዊ ገቢ ላይ የሚጨመረውን ከንብረት የሚገኘውን ገቢን ለመወሰን፡ የሁሉም ንብረት ጠቅላላ የጥሬ ገንዘብ ዋጋ ከ$5,000 ካልበለጠ በስተቀር ከንብረት የሚገኘው ትክክለኛ ገቢ ይጨምራል፡ እንደዚያ ከሆነ፡ በዓመታዊ ገቢ ላይ የሚጨመረው ከንብረቱ ጠቅላላ ዋጋ 2% ወይም ከንብረቱ ከተገኘው ትክክለኛ ገቢ ከሁለቱ ብልጫ ያለው ይሆናል።

ዓመታዊ ገቢ የሚከተሉትን ይጨምራል:

- ያልተጣራ ደመወዝ እና የሰዓት ሥራ ክፍያ በሙሉ (ከደመወዝ ክፍያ ላይ ከሚደረግ ተቀናሽ በፊት)፡ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፡ ኮሚሽን፡ የተለያየ ክፍያ፡ ጉርሻ እና ሌላ የግል አገልግሎቶች ክፍያ
- ከንግድ እንቅስቃሴ ወይም ከሙያ አገልግሎት የተጣራ ገቢ
- ከማይንቀሳቀስ ወይም ከግል ንብረት ወለድ፡ የትርፍ ድርሻና ማንኛውም ዓይነት ሌላ የተጣራ ገቢ (ንብረት የሚያካትታቸውንና የማያካትታቸውን ዝርዝር ከታች ይመልከቱ)
- በየጊዜው የሚከፈል የማኅበራዊ ዋስትና፡ ዓመታዊ ክፍያዎች፡ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች የመጦሪያ ገንዘብ፡ የጡረታ አበል፡ የአካል ጉዳት ወይም የሞት ጥቅሞች እና ተመሳሳይ ዓይነት ወቅታዊ ክፍያዎች ሙሉ ክፍያ፡ በአንድ ጊዜ የሚደረግ ወይም በየወሩ የሚደረግ ዘግይቶ የተጀመረ ጉርድ ክፍያ ማሚያን ጨምሮ ማንኛውም በየጊዜው የሚደረግ ሙሉ ክፍያ **(በተራዘመ ጊዜ ውስጥ በየጊዜው የሚከፈል ተጨማሪ የማኅበራዊ ዋስትና ተከፋይና ገቢና የማኅበራዊ ዋስትና ጥቅማ ጥቅምን አይጨምርም፡ ዓመታዊ ገቢ የማይመለከታቸውን ልዩ ሁኔታዎች ከታች ይመልከቱ)**
- በደመወዝ ምትክ የሚከፈሉ የሥራ አጥነትና የአካል ጉዳት ካሣ፡ የሠራተኛ ካሣና የአገልግሎት ክፍያ የመሳሰሉ የተለያዩ ክፍያዎች **(ከቤተሰብ ንብረት ሌላ በአንድ ጊዜ የሚደረግ ጭማሪዎችን አይጨምርም። ዓመታዊ ገቢ የማይመለከታቸውን ልዩ ሁኔታዎች ዝርዝር ከታች ይመልከቱ)**
- የችግረኛ እርዳታ
- ከፍቺ በኋላ በየጊዜው የሚከፈል አበልና የልጅ ማሳደጊያ ተቆራጭና ከድርጅቶች ወይም ከመኖሪያ ቤቱ ውጪ ከሚገኙ ግለሰቦች በየጊዜው የሚገኝ መደበኛ የመዋጮ እርዳታ ወይም ስጦታን ጨምሮ
- የጦር ኃይሎች አባል ማናቸውም መደበኛ ክፍያ፡ ልዩ ክፍያና አበል ክፍያ (ለጠላት ውጊያ ተጋላጭ ለሆኑ ልዩ ክፍያ በቀር)።
- **ለክፍል 8 ፕሮግራሞች ብቻ በ1965 የከፍተኛ ትምህርት ሕግ መሠረት ግለሰብ ከሚያገኘው የትምህርት ክፍያ የሚበልጥ ማንኛውም የገንዘብ እርዳታ የግለሰቡ ገቢ ተደርጎ ይቆጠራል፡ ሆኖም ከ23 ዓመት ዕድሜ  በላይ ለሆነ ጥገኛ ልጆች ላሉት ሰው ወይም በክፍል 8 መሠረት የገንዘብ እርዳታ የሚያገኝ ከወላጆቹ ጋር የሚኖር ተማሪ ከሆነ፡ የሚያገኘው የገንዘብ እርዳታ እንደ ዓመታዊ ገቢ የማይቆጠረውን ሰው አይመለከትም፡ በዚህ ፓራግራፍ "የገንዘብ እርዳታ" ገቢን ለመወሰን ከብድር የሚገኝ ገቢን አይጨምርም::**

ንብረት የሚከተሉትን ይጨምራል:

- አክስዮን፡ ቦንድ፡ የግምጃ ቤት ሰነድ፡ የተቀማጭ ገንዘብ የምስክር ወረቀት፡ የገንዘብ ገበያ ሒሣቦች
- የግል መጦሪያና የኬኦግ ሒሣቦች
- የመጦሪያና የጡረታ ገንዘቦች
- በቁጠባና ተንቀሳቃሽ ሒሣብ፡ በባንክ ካዝና በቤት ውስጥ ያለ ጥሬ ገንዘብ ወዘተ፡
- ከሞት በፊት በግለሰብ ሊገኝ የሚችል ሙሉ የሕይወት ዋስትዎችና ውል የጥሬ ገንዘብ ዋጋ
- ከሚከራይ ንብረት እና ከሌላ መዋዕለ ንዋይ ቀሪ አንጡራ ሀብት
- እንደ መዋዕለ ንዋይ የተያዘ የግል ንብረት

- ጥቅል ክፍያ ወይም በአንድ ጊዜ የሚደረግ ክፍያ
- በአንድ አመልካች የተያዘ የብድር መያዣ ዋስትና ወይም የንብረት መያዣ ዋስትና ሰነድ
- ከትክክለኛ የገበያ ዋጋ በታች የተሸጡ ንብረቶች ዋጋ

ንብረቶች የሚከተሉትን አይጨምሩም:
- አስፈላጊ የግል ንብረት (ልብስ፡ የቤት ዕቃ፡ መኪና፡ የጋብቻ ቀለበት፡ ለአካለ ስንኩላን የተለየ መሣሪያ የተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎች)
- ከሕንጻውያን ባለ አደራ ቦታ ጥቅሞች
- የተወሰነ ጊዜ የሕይወት ዋስትና ውሎች
- ቤተሰቡ በሚኖርበት የሕብረት ሥራ ማህበር ቤት ያለው አንጡር ድርሻ
- በሥራ ላይ ያለ የንግድ ሥራ አካል የሆነ ንብረት
- በአመልካች በባለቤትነት በትክክል ያልተያዙ ወይም በአንድ ግለሰብ ስም ያልተመዘገቡ ንብረቶች፡ ሆኖም ከሚከተሉት በስተቀር፡
  - የቤተሰቡ አባል ላልሆነ ለሌላ ሰው ጥቅም የተገኘ ንብረት ወይም ማናቸውም ገቢ፡ እና
  - ከንብረቱ ከሚመነጨው ገቢ የሚከፈለው የገቢ ግብር ኃላፊነት የሚመለከተው ሌላ ሰው ከሆነ
- ለአመልካች ተደራሽ ያልሆነና አመልካች ገቢ የማያገኝበት ማናቸውም ንብረት (ለምሳሌ፡ በባሏ በደል የደረሰባት ሚስት ከባሏ ጋር የጋራ የቤት ባለቤት ነች። ሆኖም በቤተሰቡ ውስጥ በተፈጠረው ችግር ምክንያት ከንብረቱ የምታገኘው አንዳችም ገቢ የለም፡ ንብረቱንም ወደ ጥሬ ገንዘብ መለወጥ አትችልም።)
- በሚከተሉት ምክንያቶች ከትክክለኛው የገበያ ዋጋ በታች የተሸጡ ንብረቶች፡
  - በብድር ዕዳ አለመክፈል የቤት መወሰድ
  - ዕዳ ለመክፈል ባለመቻል በኪሳራ
  - በፍቺ ወይም በመለያየት ስምምነት አመልካች ወይም ነዋሪ በጥሬ ገንዘብ ባይሆንም ሌላ ዋና ማካካሻ ካገኘ።

እንደ ዓመታዊ ገቢ የማይቆጠሩ ሁኔታዎች:
- ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ ልጆች የቅጥር ሥራ የሚገኝ ገቢ (ከጉዲፈቻ ልጆች ጭምር)
- ለጉዲፈቻ ልጆች ወይም ለጉዲፈቻ አዋቂዎች (ብዙውን ጊዜ አካለ ስንኩላን የሆኑ፡ ከተከራይ ቤተሰብ ጋር ዝምድና የሌላቸውና ለብቻቸው መኖር የማይችሉ ሰዎች) እንክብካቤ የሚገኝ ክፍያ
- እንደ ውርስና የኢንሹራንስ ክፍያዎች ያሉ፡ (በጤና እና በአደጋ በሚደርስ ጉዳት የኢንሹራንስ ዋስትና መሠረት የሚከፈል የሠራተኛ የጉዳት ካሣ ክፍያዎችን ይጨምራል)፡ የካፒታል ትርፍና ለግል ዕቃና እና የንብረት ጥፋት ክፍያን ጨምሮ በቤተሰብ ንብረት ላይ የሚደረግ የአንድ ጊዜ ጭማሪዎች
- ቤተሰቡ በተለይ ለማንኛውም የቤተሰቡ አባል ያወጣውን የሕክምና ወጪዎችን ለመተካት በቤተሰቡ የሚያገኝ ተመላሽ ክፍያ
- በቤተሰቡ ውስጥ እየኖረ የሚረዳ ሰው ገቢ
- **በክፍል 8 ፕሮግራም መሠረት የከፍተኛ ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች የሚያገኙት ገቢ ከላይ በተገለጸው በዓመታዊ ገቢ የሚካተት እስከሆነ ድረስ **ሙሉ ለተማሪ በቀጥታ የተከፈለም ይሁን ወይም ለሚማርበት የትምህርት ተቋም የተከፈለ የተማሪ የገንዘብ እርዳታ
- በጦር ኃይሎች ለሚያገለግል ለጠላት ተኩስ ተጋላጭ ለሆነ የቤተሰብ አባል፡ ለቤተሰቡ የሚሰጥ ልዩ ክፍያ
- በኤችዩዲ የገንዘብ እርዳታ ከሚካሄድ የሥልጠና ፕሮግራም የተገኘ ክፍያ
- ራስን ብበደረሰ የአካል ጉዳት ምክንያት የሥራ ችሎታ በማጣታቸው ከሥራ የተሰናበቱ ሰዎች ተጨማሪ የማኅበራዊ ዋስትና መብት ተጠቃሚ እስከሚሆኑ ድረስ ራስን በማስቻል ፕሮግራም (ፒኤኤስኤስ) አማካይነት ለተወሰነ ጊዜ የተገኘ ገቢ
- በመንግሥት በሚረዱ ሌሎች ፕሮግራሞች ተሳታፊ የሆኑ ሰዎች ከኪሳቸው ላወጡት ክፍያ (በተለይ ለልዩ መሣሪያ፡ ልብስ፡ ትራንስፖርትና የልጅ እንክብካቤ ወዘተ) እና በልዩ ፕሮግራም ለሚያደርጉት ተሳትፎ ብቻ የሚያደረጉ ተመላሽ ክፍያ።
- የነዋሪዎች አገልግሎት የኪስ ገንዘብ (በወር ከ$200 የማይበልጥ)
- ማንኛውም የቤተሰብ አባል ለስቴት ወይም ለአካባቢ ሥራ የሥልጠና ፕሮግራምና ለነዋሪዎች አስተዳደር ሠራተኝነት ለመወዳደር ከሚያደርገው ተሳትፎ የሚያገኝ ጭማሪ ገቢና ጥቅማ ጥቅም
- ጊዜያዊ ወይም ተደጋጋሚ ያልሆነ ወይም አልፎ አልፎ የሚገኝ ገቢ (ስጦታዎች ጭምር)
- በናዚ ዘመን ጊዜ በአገራቸው ይፈጸምባቸው ከነበረው ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት በመሸሽ በስደት ላይ የሚገኙ ስደተኞችን በመንግሥት በተደነገገው ሕግ መሠረት ወደ መጡበት አገር ለመመለስ በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት በውጪ አገር መንግሥት የሚከፈል ካሣ ክፍያ።
- ዕድሜው ከ18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ እያንዳንዱ ተማሪ የሚያገኘው ከ$480 የሚበልጥ የገንዘብ እርዳታ(የቤተ ሰብ አላፊ፡ ወይም የጋራ አላፊ ወይም ባለቤት)
- ለአንድ ልጅ ጉዲፈቻ ከ$480 በላይ ለሆነው ክፍያ የጉዲፈቻ እርዳታ

- ሁሉንም በአንድ ጊዜ ወይም በየወሩ የሚደረግ ተጨማሪ የማኅበራዊ ዋስትና ገቢ እና የማኅበራዊ ዋስትና ጥቅማ ጥቅም ተላላፊ ክፍያዎች
- በስቴት ወይም በአካባቢው ሕግ መሠረት ለመኖሪያ ቤት በሚከፈለው የንብረት ታክስ ላይ በተመላሽ ወይም በቅናሽ መልክ ለቤተሰቡ የሚደረግ ክፍያ
- የእድገት ዝግመት እክል ያለበት የቤተሰብ አባል ያለው ቤተሰብ አባሉ ቤተሰቡ ውስጥ እንዲኖር ለማድረግ ልዩ ፍላጎቶቹን ለማሟላት የሚያስፈልገውን የአገልግሎትና የመሣሪያ ወጪ ለመሸፈን በስቴት ድርጅት ለቤተሰቡ የሚያደርገው የገንዘብ ክፍያ

በፌዴራል ሕግ የማይፈቀዱ ሁኔታዎች፡

- በ1977 የምግብ ቴምብር ድንጋጌ መሠረት ለምግብ እርዳታ ብቁ ቤተሰቦች የሚሰጥ እርዳታ ዋጋ
- በ1973 የአገር ውስጥ የበጎ ፈቃደኞች አገልግሎት ድንጋጌ መሠረት የበጎ ፈቃደኞች ክፍያ
- በአሳስካ ተወላጆች የካሣ ጥያቄ ድንጋጌ መሠረት የሚገኝ ክፍያ
- በአንዳንድ የሕንድ ጎሣ አባላት ከተያዘ የዩናይትድ ስቴትስ ዳርቻ መሬት ባለአደራ የሚገኝ ገቢ
- በጤናና ሰብዓዊ አገልግሎት ክፍል አነስተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች የኃይል ድጋፍ ፕሮግራም መሠረት ተጠቃሚዎች የሚያገኙት ክፍያና አበል
- በሙሉም ሆነ በከፊል የገንዘብ እርዳታ በሥራ ሥልጠና ሽርክና ድንጋጌ መሠረት በሚገኝ ክፍያ
- ለኦታዋ ሕንዳውያን ግራንድ ሪቨር ባንድ ከሚደረግ ክፍያ የሚገኝ ገቢ
- በባለ አደራ ሥር ወይም በተከለከሉ ቦታዎች የሚገኙ ግለሰብ ሕንዳዊያን በሕንዳዊያን የካሣ ኮሚሽን ወይም በዩኤስ የካሣ ፍርድ ቤት ከተፈረደባቸው ካሣ በነፍስ ወከፍ በሚያገኙት የመጀመሪያው የ$2000 የካሣ ክፍያ፡ በእነዚህ ባለአደራዎች ወይም በተከለከሉ ቦታዎች የሚገኙ ግለሰብ ሕንዳውያን በነፍስ ወከፍ በሚያገኙት ገንዘብ ላይ በያመቱ የሚታሰብ የመጀመሪያውን $2000 ወለድ ይጨምራል።
- በፌዴራል የሥራ - ጥናት ፕሮግራም ወይም በሕንዳውያን ጉዳይ ቢሮ የተማሪዎች የድጋፍ ፕሮግራም ሥር የሚሰጠውን ጨምሮ በ1965 የከፍተኛ ትምህርት ድንጋጌ ርዕስ 4 መሠረት በሚደረግ የገንዘብ እርዳታ የሚሰጥ የትምህርት ክፍያ
- በ1985 አረጋውያን አሜሪካውያን ሕግ ርዕስ 4 መሠረት የገንዘብ እርዳታ ከሚደረግላቸው ፕሮግራሞች የሚገኝ ክፍያ
- ከኤጀንት ኦሬንጅ የካሣ ክፍያ ገንዘብ ወይም በኤጀንት ንጥረ ነገር ኃላፊነት ክርክር የካሣ ክፍያ መሠረት ከተቋቋመ ማካካሻ ወይም ከማንኛውም ሌላ ገንዘብ ጃንዋሪ 1 ቀን 1989 ወይም ከዚያ በኋላ የተገኘ ክፍያ
- በሜይን የሕንዳውያን የካሣ ክፍያ የ1980 ሕግ መሠረት የሚገኝ ክፍያ
- በ1990 የልጅ እንክብኮቤና ልማት ጥምር ስጦታ ሕግ መሠረት ለማንኛውም ልጅ የተሰጠ ወይም የተመቻቸ የእንክብካቤ አገልግሎት ዋጋ (ለእንክብካቤው ለተደረገ ወጪ የተደረገውን ክፍያ ወይም ማናቸውንም ተመላሽ ክፍያን ይጨምራል)
- ጃንዋሪ 1 ቀን 1991 ወይም ከዚያ በኋላ ለተገኘ ገቢ በቅድሚያ የተከፈለ የገቢ ግብር (ኢአይቲሲ) ክፍያ ተመላሽ
- በሕንዳውያን የካሣ ኮሚሽን ለያኪማ ሕንዳውያን ዜጋ ወይም ለማስካሬሎ ሪዘርቬሽን የአፓቼ ጎሣ ኮንፌዴሬትድ ጎሣዎች ጥምር የተከፈለ የካሣ ክፍያ
- በ1990 የብሔራዊና የማኅበረሰብ አገልግሎት ሕግ መሠረት ለአሜሪኮር ተሳታፊዎች አበልና ክፍያ
- በ38 ዩኤስሲ 1805 ድንጋጌ መሠረት ከቬትናም ዘማቾች የተወለዱ በስፓይና ቢፊዳ ሕመም የሚሰቃዩ ልጆች የሚያገኙት ማንኛውም የአበል ክፍያ
- በወንጀል ሰለባዎች እርዳታ በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት (በወንጀል ሰለባዎች ድጋፍ ሕግ መሠረት) ከወንጀል ሰለባዎች እርዳታ የሚገኝ (ክፍያ ወይም የወጪ ተመላሽ) በወንጀል ሰለባዎች ድጋፍ ሕግ ውንጀል ስለተፈጸምባቸው የሚወሰን የወንጀል ሰለባዎች ማናቸውም መጠን የካሣ ክፍያ
- በ1998 የሥራ ኃይል ልማት ሕግ መሠረት ለሚሳተፉ ግለሰቦች የሚደረግ አበልና ክፍያ
- በ2008 የቤቶችና የኢኮኖሚ ተሃድሶ ሕግ (ኤችኢአርኤ) ግዴታን ለማሟላት በአባት ጦር ጉዳይ ክፍል ለአካለ ስንኩላን በአንድ ጊዜ ወይም በየወሩ ለተከራይ የሚከፈል የተራዘመ የጥቅማ ጥቅም ክፍያ

## ተቀናሾች:

- ለእያንዳንዱ ጥገኛ ለሙሉ ጊዜ ተማሪ ወይም ማንኛውንም አካለ ስንኩል ጨምሮ $480
- ለማንኛውም አረጋዊ ቤተሰብ ወይም አካለ ስንኩል ቤተሰብ $400
- ለማንኛውም አረጋዊ ወይም አካለ ስንኩል የቤተሰብ አባል ከጠቅላላ ዓመታዊ ገቢው ከ3% በላይ የሕክምና ወጪ ተመላሽ ያልተደረገ ክፍያ

- ቤተሰቡ ተቀባይነት ሳለው የአካል ጉዳተኛ የቤተሰብ አባላት እንክብካቤና አስፈላጊ ዕቃዎች ሳወጣው የቤተሰብ አባላት እንዲሠሩ የሚረዳ ድጋፍ ወጪ ከጠቅላላ ዓመታዊ ገቢው ከ3% በላይ የወጪ ተመላሽ
- አንድ አረጋዊ የቤተሰብ አባል የሕክምና ወጪ ተመላሽና የአካል ስንኩልነት የወጪ እርዳታ ሁለቱንም ካገኘ የቤተሰቡ ገቢ 3% ወጪ ለአንድ ጊዜ ብቻ ይሠራበታል
- ዕድሜያቸው ከ13 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ወደፊት ሥራ እንዲያገኙ ወይም ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ለመርዳት የሚደረግ ተቀባይነት ሳለው እንክብካቤ የሚከፈል ማናቸውም የወጪ ተመላሽ።

## ማጣቀሻ ጽሑፎች

ደንቦች:

- General HUD Program Requirements; 24 CFR ክፍል 5

የእጅ መጽሐፍ:

- 4350.3, Occupancy Requirements of Subsidized Multifamily Housing Programs

የሕዝብ ማስታወቂያ:

- “Federally Mandated Exclusions” Notice 66 FR 4669, April 20, 2001

መረጃ ለማግኘት:

የኤችዩዲ ፕሮግራሞችን በሚመለከት ተጨማሪ መረጃ በኤችዩዲ ኢንተርኔት የውስጥ ገጽ+ አድራሻ http://www.hud.gov ማግኘት ይቻላል።